የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አንደኛ ዓመት ቁጥር ፵፱
አዲስ አበባ ሀምሌ ፳፬ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

21[st] Year No. 49
ADDIS ABABA 31[st] July, 2015

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፰፻፺፯/፪ሺ፯ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በግብጽ አረብ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል የተደረገው የንግድ ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ................ገጽ ፰ሺ፪፻፶፰

CONTENTS

Proclamation No. 897/2015

The Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Arab Republic of Egypt Trade Agreement Ratification Proclamation........................................Page 8258

## አዋጅ ቁጥር ፰፻፺፯/፪ሺ፯

**<u>በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በግብጽ አረብ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል የተደረገው የንግድ ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ</u>**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በግብጽ አረብ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል የተደረገው የንግድ ስምምነት ጥቅምት ፳፬ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመ ስለሆነ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፲፩ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም ባካሄደው መደበኛ ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራስያዊ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## PROCLAMATION No.897/2015

**<u>A PROCLAMATION TO RATIFY TRADE AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE GOVERNMENT OF THE ARAB REPUBLIC OF EGYPT</u>**

WHEREAS, the Trade Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Arab Republic of Egypt was signed in Addis Ababa, on the 3[rd] day of November,2015;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified this Agreement at its session held on the 18[th] day of June, 2015;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በግብጽ አረብ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል የተደረገው የንግድ ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፰፻፺፯/፳፻፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**፪. የስምምነቱ መፅደቅ**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በግብጽ አረብ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል ጥቅምት ፳፬ ቀን ፳፻፯ ዓ.ም አዲስ አበባ ላይ የተፈረመው የንግድ ስምምነት ፀድቋል።

**፫. የንግድ ሚኒስቴር ስልጣን**

የንግድ ሚኒስቴር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ይህን ስምምነት በሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ ስልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል።

**፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ሀምሌ ፳፬ ቀን ፳፻፯ ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**
**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as "the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Arab Republic of Egypt Trade Agreement Ratification Proclamation No.897/2015".

**2. Ratification of the Agreement**

The Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Arab Republic of Egypt Trade Agreement Ratification Proclamation signed in Addis Ababa on the 3rd day of November, 2014 is hereby ratified.

**3. Power of the Ministry of Trade**

The Ministry of Trade in Collaboration with the relevant organs is hereby empowered to implement this agreement.

**4. Effective Date**

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 31st day of July, 2015.**

**MULATU TESHOME (DR.)**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት